የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዚያ /2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ቁጥር	ርእስ/ንኡስ ርእስ	ገፅ
ክፍል አንድ	መግቢያ	3
1.1.	የጥናቱ ዳራ (Backgraound Of The Study)	3
1.2.	የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ	4
1.3.	የጥናቱ ዓላማ	5
1.4.	የጥናቱ ወሰን	5
1.5.	የጥናቱ አስፈላጊነት	6
1.6.	መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች	6
ክፍል ሁለት	ተዘማጅ ፅሁፎች ትንተና	7
ክፍል ሶስት	የጥናቱ መረጃ አሰባስብ ሂደትና ትንተና ዘዴ	8
3.1.	የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)	8
3.2.	የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)	8
3.3.	መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)	8
3.4.	የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ	9
ክፍል አራት	የሙስና ስጋት ትንተና	10
4.1.	የተቋማት አደረጃጀት	10
4.2.	ተጠያቂነትን ማስፈን	13
4.3.	የተቋማት ግልጽነት	14
4.4.	አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ	16
4.5.	የተቋማት ንብረት አስተዳደር	18
4.6.	የግዥ አስተዳደር	19
4.7.	የሰው ሃብት አስተዳደር	20
4.8.	የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ	22
4.9.	ኦዲትና ቁጥጥር	22
4.10.	የሙስና ስጋት	23
ክፍል አምስት	መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	25
5.1.	መደምደሚያ	25
5.2.	የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	26

ክፍል አንድ

መግቢያ

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት በኢንዱስትሪ ዘርፍ ስር የሚገኙ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትየጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተቋማት ላይ የተካሄደ ሲሆን በአምስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡

1.1. የጥናቱ ዳራ

ሙስና በአደራ የተሰጠ ስልጣንና ኃላፊነትን ያለ አግባብ በመገልገል የህዝብና የመንግስት ሁለንተናዊ ስርዓትን የሚያዛባና ፍትህን የሚሸረሽር ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል በመሆኑ ሀገራት ይህን ወንጀል መከላከል የሚያችል ዓለማቀፋዊ፣ አህጉራዊና ቀጠናዊ ቅንጅትና ትብብር በመፍጠር በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት ይህን ወንጀል መከላከል የሚያስችል የትኩረት አቅጣጫ በመቀየስ በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን የፌደራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽንም ከመንግስት የተሰጠውን ተልዕኮ ማሳካት የሚያስችሉ ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስልቶችን በመንደፍ እየሰራ ይገኛል፡፡ ከዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከያ ስልቶች አንዱ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት አንዱ ነው፡፡ ተቋማት የአሰራር ስርዓት ቢዘረጉም፣ በየጊዜው ደንብና መመሪያ የሚያሻሽሉ ቢሆንም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንጻር እዚህ ግባ የሚባል ለውጥ ማምጣት አልቻሉም፡፡

እንደማሳያ ማህበረሰቡ በመንግሰት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ እያሰማ መሆኑ፣ ዜጎች በመንግስት ተቋማት አመኔታቸው እየቀነሰ መምጣቱ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ መጓተት፣ ተደጋጋሚ ኦዲት ግኝቶ መበራከትና የመሻሻያ ሀሳቦችን አለመተግበር፣ የገበያ ስርዓቱ የተረጋጋ አለመሆንና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የግዥ ዘዴን አለመጠቀም፣ የተጠያቂነት ማነስ ጥቂት ማሳያዎች ናቸው፡፡ በመንግስት ተቋማት ለሚታዩት የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ማነስ፣ የህግ የበላይነት ድክመት፣ ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር ፣ የግልፅነትና ተጠያቂነት ክፍተቶች መበራከት እንደመንስኤ የሚነሱ ናቸው፡፡

በዚህ ምክንያት የፌደራል የስነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ በተደነገገው መሰረት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትየጵያ ኢንተርፕርይዝ ልማት እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አሰራርና አደረጃጀት፣ የተጠያቂነት ስርዓት፣ የተቋማት ግልፅነት፣ የአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ዝግጅትና ትግበራ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር፣ የግዥ አስተዳደር፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ የኦዲትና ቁጥጥር ሥርዓትክ ፍተቶችን በመፈተሽ፣ የሙስና ስጋቶችን በመለየትና የማሻሻያ ምክረሃሳብ በማቅረብ የአሰራር ስርዓት እና የፖሊሲ ማሻሻያ ግብዓቶች ማመንጨት ዓላማ አድርጎ ይህ ጥናት በኢንዱስትሪ ዘርፍ ስር በሚገኙ ተቋማት ላይ ተጠንቷል፡፡

1.2. የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ

በኢንዱስትሪ ዘርፍ "በ2022 የአምራች ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት" የሚል ርዕይ ያለው ሲሆን በስሩ የሚከተሉት ተቋማትን ያካትታል፡፡ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትየጵያ ኢንተርፕርይዝ ልማት እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሲሆኑ የተመሰረቱበት የጊዜ አማካይ ከ1950ዎቹ ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ ያለውን የሚያካትት ሲሆን በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት 1,968 ቋሚ ሰራተኞችን በመያዝ ርዕዩን ለማሳካት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ዘርፉ የተደራጀበት ዋና ዓላማ አምራች ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲወጣና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሳደግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣መመሪያዎችን እና የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 መሰረት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

- በኢንዱስትሪ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤
- በኢንዱስትሪ በተለይም ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት ትኩረት የሚሠጣቸውን ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ እና የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪዎችና የመሳሰሉት ንዑስ ዘርፎች ካላቸው አንጻራዊ ጠቀሜታና እምቅ አቅም አኳያ ይለያል፤ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በዘርፉ ምርምርና ጥናት የሚያካሂዱ አካላትን አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የኢንዱስትሪዎችን፣ የኢንቨስትመንት እና የማኑፋክቸሪንግ አቅምና ተወዳዳሪነትን እንዲያድግ ያደርጋል፤ሠ) በኢንቨስትመንት ሕግ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ በሥሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤
- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን፤ የምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ እና አጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤
- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤
- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንዱስትሪ በተለይም ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል ፍላጎት እና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ ከሚመለከተው ዘርፍና አካላት ጋር በመሥራት የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

- ለዘርፉ እድገት ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ ስለሚመጣበት ሁኔታ ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ለማዕድን ሚኒስቴር ከተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ የኢንዱስትሪ ገቢ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ ድጋፍ ያደርጋል፤
- በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤
- የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ውጤታማ እንዲሆኑ የማትጊያ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤
- የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፤
- የኢንዱስትሪ፣ የዘርፉ እና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታተል፣ የተቋቋሙትንም እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡

1.3. የጥናቱ ዓላማ

አጠቃላይ ዓላማ፡-

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመገምገም የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

ዝርዝር አላማዎች፡-

- የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ከህዳር/06/2015ዓም እስከ ሚያዚያ/30/2015ዓም በኢንዳስቲሪ ሚኒስቴር፣ በአምራች ኢንዳስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ

ልማት ተቋማት ላይ ተቋማዊ ተጠያቂነት፣ ግልፅነት፣ አዋጅ ደንብና መመሪያ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር የግዥ አስተዳደር፣የሰው ሃበት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና ኦዲትና ቁጥጥር የአሰራር መርሆችን መሰረት በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በአሰራር እና የስራ ሂደቶች ውስጥ የሚታዩ ድክመቶችና ብልሽቶች በመለየት የሙስና ቅደመ መከላከል እድል ስራዎች ለመተግበር የሚግዝ መሳሪያ ነው፡፡ ዋናው የግምገማዊ ጥናቱ አላማም የሙስና ስጋቶች በተጨባጭ መረጃ በተደገፈ በመለየት የመከላከል ስልቶችን እና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ማስቻል ነው፡፡ እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ የአደጋ ለውጦችን ለመከታተል ለፀረ-ሙስና ትግል ሥራ እንደ መነሻ ሆኖም ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዚህ መሻነት ይህ ጥናት በማዕድን ዘርፍ የሚታዩ የሙሰና ስጋቶች በአስራ አንድ የትኩረት ጉዳዮች ለመየት የተካሔደ ነው፡፡ ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ፋይዳው በኢንዱስተሪ ዘርፍ የሚሰሩ መንግስታዊ ተቋማት የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የስራ ዘርፎችንና የአሰራርር ስርዓቶችን በመለየት፣ የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ በማመንጨት የሙስና መከላከል ስልት ማመላከት እና በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

1.6. መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

የጥናት ሥራው የተካሄደው ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሠራር ከመከላከል ረገድ ሊያከናዉኗቸው የሚገቡ ተብለው በተለዩ የትኩረት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሲሆን በተጠየቁት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን የተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በመጠየቅ መረጃ ሲበሰብ አንዳንድ ተቋማት ውስጥ የሚፈለጉና መረጃ የሚሰጡ የሥራ ኃላፊነት በቀጠሮ ምልልስ ማጋጠሙ፣ በተቋማት መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅቶ ባለመያዝ በተናጠል ለመሰበሰብ መቸገር፣ ሥራውን የሙስና ወንጀል ምርመራ አድርጎ በመውሰድ መረጃ ለመስጠት የማንገራገር ሁኔታዎች በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ተግደራቶች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

የተዛማጅ ፅሁፎች ትንተና

ሙስና አንድን ምጣኔ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያደርሰው ሁሉ በማምረቻ ተቋማት ልማትና እድገት ተመሳሳይ ተፅእኖ አለው፡፡ በዋናነት በዘርፉ ያለው የመወአለ ንዋይ ፍሰት እንዲቀንስ በማደረግ በኩል ሙስና በተለይ ጉቦ መስጠትና መቀበል የሚጫወተው ሚና እንዳለው ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ የመንግሰት ባለስልጣናት ሰራተኞች የተሰጣቸውን የመወሰን ስልጣን በመጠቀም እጅ መንሻ በመቀበል በፍቃድ አሰጣጥ ላይና ገበያ ውድድር ላይ በጎ ያልሆነ ተፅእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ (Chakravorty, Rutskiy & Sevastyanova, 2022) ፡፡ በታዳጊ አገሮች ሙስና በዋናነት የሚመነጨው ከተቋማዊ ጎድለቶች የሚመነጭ ነው፡፡ መደበኛ የመከላከል ስራው ከተቋማዊ ጉድለት አንፃር አለመመጣጠን ሲከሰት ለሙሰና በር ይከፍታል፡፡ መደበኛ አሰራር የሚፈጥረው ቢሮከራሲያዊ መሰላሎቸን ለማለፍ ኢመደበኛ የሆነው አሰራር እንዲፈጠር በማደረግ ሙስና በመንግስት ተቋመት ውስጥ የመከሰት እድሉ ያሰፋዋል፡፡ ይህም የማምረቻ ድርጅቶች ኢመደበኛ መንገድ ተጠቅመው ለመወዳደር ሲሞከር ለባለስልጣናት ኪራይ የማካፋል ውስጥ መግባታቸው የሚጠበቅ ይሆናል፡፡ ውድድሩ ገበያ መር ስለማይሆን በድርጅት አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ሚና ሊኖረው እንደሚችል ነው (Williams and Martinez-Perez, 2016)፡፡

በማምረቻ ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ብዙ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ጉቦ መስጠት፣ የኢኮኖሚ ማዕቀቦች ጥሰት፣ የኤክስፖርት ቁጥጥር ጥሰቶች እና የታክስ ስወራ የመሳሰለሉ ለኢኮኖሚያዊ ወንጀሎች የሚፈፀምበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ እንዲሁም እንደ ዘመናዊ ባርነት እና የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ያሉ ሰፊ ማህበራዊ ጉዳዮችን በመጣስ ሌላ ማህበራዊ ቀውስ የማስከተል እድል አለው፡፡ በዚህ መንገድም በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን ጥረት ይደረጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ጤናማ የገበያ ውድድር እንዲፈጠር በማደረግ መንግሰተት ገቢ ሊያጣ መቻሉ በተጨማሪም ማህበረሰቡን ለብዝበዛ ሊያጋልጠው ይችላል (Deloitte LLP, 2020) ፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ሙስና በአለማቀፍ የሚደረገው የንግድ ውድድርም ላይ አሉታዊ ጥላ ሊያጠላበት እንደሚችል እሙን ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ሙስና ለንግድና ኢንቨስትመንት እንቅፋት በመሆን ፍሰቱን ያልተፈለገ ቅርፅ እንዲይዝ የማድረግ አስተዋፅኦ ሊኖረው መቻሉ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ የሙስና አሉታዊ ተፅዕኖ ከሚያሳዩ ጉዳዮች አንዱ ከአደጉ አገሮች የሚመጡ

የንግድ ድርጅቶች በአላደጉ አገሮች ላይ ገበያ ለማግኘት በማሳብ የተላያዩ የሙስና ዘዴዎች በጠቀም የገበያው መዋቅራዊ ይዘት ላይ አሉታዊ ሚና ሊጫወቱ ይቻላሉ (Tingvall, 2010)፡፡

1.

ክፍል ሶስት

የጥናቱ መረጃ አሰባስብ ሂደትና ትንተና ዘዴ

3.1. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)

ሙስናና ብልሹ አሠራር ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚያደርሰውን የሙስና ሥጋት ጥናት ለማካሄድ በአብዛኛው ዓይነታዊ እና በተወሰነ ደረጃ የአሃዛዊ (mixed approach) የጥናት ዘዴዎችን በማጣመር በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆነው መረጃም ከየካቲት 8 እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም የመሰብብ ስራ ተሰርቷል፡፡

3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)

ይህ ጥናት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣ የህግ አገልግሎት፣ የለውጥና መልካም አስተዳደር፣ የአይሲቲ የጥናት መረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዘዴ ከወሳኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች መካከል የሆነውን ዓላማ ተኮር ዘዴን በመከተል የጥናቱ ተሳታፊዎችን የለየ ሲሆን በተቋማት ውስጥ ባሉ አሠራሮችና የስራ ሂደቶች ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሄደ ጥናት ነው፡፡

3.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)

3.3.1. የዝግጅት ምዕራፍ

በዚህ በዘርፍ ሥር በተደራጁት ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 11 የትኩረት ርእሰ ጉዳዮችን የመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የመረጃ መሰብሰቢ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በመጠይቅ ዙርያ ላይ ለመረጃ ሰበሳቢዎች ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎችም ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎች ለመሰብሰብ እንዲቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ በመፍጠር መረጃ

የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለጥናቱ ግብኣት የሚሆነው መረጃ የተሰበሰበባቸው የትኩረት ርዕሰ ጉዳዮችም ዝርዝር በሚቀጥለው ንኡስ ርእስ ቀርቧል፡፡

3.3.2. የሙስና ሥጋት መንስኤዎችንና አመላካቾችን ልየታ

የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ሲዘጋጅ ታሳቢ የተደረገው በተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት ሊያሳዩ የሚችሉ አመላካች ርዕሰ ጉዳዮች መለየት ነው፡፡ በዚህ እሳቤ መነሻነትም አስራ አንድ ተለየይተው የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቁ ተዘጋጅቷል፡፡ በዘርፉ በተደራጁት ተቋማት የትኩረት ርዕሰ ጉዳዩ ባለመከናወኑ ወይም ሲከናወን የተስተዋሉ ችግሮችን ከሙስና እና ብልሹ አሠራር አንፃር በመቃኘት የሙስና የስጋት መንስኤዎች ወይም አመላካች መረጃዎች መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያው መጠይቅ ውስጥ የተካተቱ ትኩረት የተሰጣቸው ርዕሰ ጎዳዮች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ተቋማዊ አደረጃጀት፡-** ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አስራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ተጠያቂነት፡-** ተቋማት ተልዕኳቸውን የህግ የበላይነትን በማረጋገጥና ተጠያቂነትን ለማስፈን የህግ ጥሰቶችን በህግ ስርዓት በማስተካከል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ግልፅነት፡-** የመንግስት ተቋማት የተቋቋሙበት ዋና አላማ ለህዝብ አገልግሎት መስጠት እስከሆነ ድረስ ተግባር፣ሃላፊነታቸውና የአሰራር ስርዓታቸውን ለተገልግጋዩ ማህበረሰብ ግልፅና ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት አገልሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተደራሽነት መርሆች ምን እደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ፡-** ሙስና እና ብልሹ አሰረሰርን ለመከላከል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣አፈፃፀምንን ለማሻሻል ተቋማት የአሰራር መመሪያ፣ አዋጅና ደንብ ያወጣሉእንዲሁም በየ ጊዜው ያሻሽላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት ቁመና ምን እንደምሚስልና የሚያወጧቸው የአሰራር መመሪያዎች ምን ያክል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ስለመናቸው የምንፈትሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

- **ተቋማዊ ንብረት አስተዳደር፡-** የዘርፉ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡም ሆነ አገልግሎት የማይሰጡ፣ መወገድና መጠበቅ ያለባቸው የተቋማት ንብረቶች የተያዙበት ስርዓት ምን እንደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የግዥ አስተዳደር፡** ግዥ በእቅድ፣በመመሪያና በቴክኖሎጅ በታገዘ መልኩ በመፈፀም ብልሹ አሰራርን የሚከላከሉበትን ስረዓትና አሰራር የመፈተሽበት የጥኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሰው ሃብት አስተዳደር፡** አቅምና ብቃት ያለው የሰውሃበት መረጃ አያያዝን እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ የሚያስተዳድሩብትን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሀብት ምዝገባ፡ ሀብት** ምዝገባ አንዱ የግልፅነትና ተጠያቂነት ማረጋገጫ መርህ ስለሆነ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሀብታቸውን ስለማስመዝገባቸው የምንፈሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ፕሮጀክት አስተዳደር፡** ተቋማት የሚያስተዳድሯቸውን ፕሮጀክቶች የሚያስተዳድሩበትና የሚቆጣጠሩበት ስርዓት ብክነትን በቀነሰ እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ስለመሆኑ የምንገመገምበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የኦዲት ቁጥጥር፡** የውስጥና የውጭ የኦዲት ግኝቶችን የሚገመገሙበት፣ ውይይት የሚደረግበት እንዲሁም የማስተካያ አስራሩ ምን እንደሚመስል ተቋማት የሚገመገምበት የትኩረት መስክ ነው
- **የተቋማትን ልዩ ተልዕኮ መሰረት ያደረገ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ልየታ፡** ተቋማት የጋራ ከሚያደርጓቸው የድጋፍ የስራ ክፍሎች በተጨማሪ የተቋቋሙት ልዩ ተልዕኮ ያላቸውን የተጋላጭነት ሁኔታ የተለየ የሚያደርገው በመሆኑ ልዩ የሆኑት የሚታዩበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

3.4. የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ

የተሰበሰበው መረጃ ከመተንተቱ በፊት ከየተቋማቱ መረጃዎች በርእሰ ጉዳች ከተለዩ በኋላ የማደራጃት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከተደራጀው የሰነድ መረጃ ለማውጣት (extract) እንዲቻል በየዘርፉ የጥናት ቡድኖች ተዘጋጅተው ስራው እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ መረጃው በማውታት ሂደትም በተለዩት ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ ተቋማቱ ማከናወን ሲገባቸው ያለከናወኑት ተግባር፣

ተግባራቱን ሲያከናወኑ የተስተዋሉ ችግሮችንና ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም በተግባራት ክንውን ወቅት የተስተዋሉ ለሙስና የተጋለጡና ብልሹ አሰራሮች ለመለየት አስችሏል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለመተንተን እንዲቻል ከአሉት ዓይነታዊ መረጃ አተናተኖች ውስጥ ጭብጥ ተኮር (Thematic Analysis) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ሪፖርት አቀራረብም አይነታዊ ገለፃ ዘዴ (Descriptive Method) ተግባራዊ የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በትንተናው ሂደትም መረጃዎች በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ተግዳረቶች ግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡ ይህም ድምዳሜ ላይ ከመድረሳችን በፊት ጥንቃቄ እንድናደርግ ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

ክፍል አራት

የሙስና ስጋት ትንተና

የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ጥናት ትንተና ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የተጠያቂነት ስርዓት፣ የተቋማት ግልፅነት፣ የአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ዝግጅትና ትግበራ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር፣ የግዥ አስተዳደር፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና የኦዲት ቁጥጥር የአሰራር ሥርዓት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትየጵያ ኢንተርፕርይዝ ልማት እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተቋማቶችን አፈፃፀም በመዳሰስ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ማስታወሻ፡ ከኢትየጵያ ኢንተርፕርይዝ ልማት በስተቀር ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተቋማት በ2014 ዓ.ም የተቋቋሙ መሆናቸውን ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው፡፡

4.1. የተቋማት አደረጃጀት በተመለከተ

በኢንዱስትሪ ዘርፍ ስር ያሉት ሶስቱም ተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸውን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት አቋቁመዋል፡፡ በዘርፉ ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ከተፈቀዱ የስራ መደቦች በአማካይ 90 በመቶ የሚሆኑት የስራ መደቦች በሰው ሃይል ተሟልቷል፡፡ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ እቅድ በማዘጋጀትና ዕቅዳቸውን መሰረት በማድረግ እንደሚሰሩ እና ምቹ የስራ ቦታ እዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እንደተሟሉላቸው በተደገ ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በጀትን አጠቃቀምን በሚመለከት የስራ ክፍላቸው ቁርጥ በጀት (ራሱን የቻለ

የበጀት አርዕስ ይዞ የተመሳካተ) አይኑር እንጅ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን በወጭ ፕሮፖዛል በሚጠይቁበት ወቅት የሚፈቀድበት አሰራር (ፑል ሲስተም) በሁሉም ተቋማት እየተተገበረ እንደሆነ የሰነድ ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ከሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል በተጨማሪ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የስርዓተ ጾታ፣ የህግ ክፍል፣ የግዢ ኮሚቴ፣ ተቋማዊ ለዉጥ የሥራ ክፍሎች፣ ወዘተ መደራጀታቸዉን ከቀረቡ መረጃዎችና በተረደጉ ምልከታዎች ማረጋገጥ ቢቻል በዘርፉ ስር ከሚገኙ ከሶስቱ ተቋማት በአንዱ ከአደረጃጀት ባሻገር በህግ ክፍል ስራ መደብ የሰዉ ሃይል ያልተመደ መሆኑ እንደጉድለት ታይቷል፡፡

የጥቆማ መቀበያ ስርዓት የተከሰቱ የሙስና ድርጊቶች እና ብልሹ ተግባራትን ለመለየት፣ ለማጣራት እና ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ አይነተኛ የትግል መሳሪያ ነው፡፡ በዘርፉ ስር በሚገኙ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ የሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ኢሜይል፣ ድረ-ገጽ እና ስልክ የመሳሰሉት ዘመናዊና ተደራሽ የጥቆማ መስጫ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

በዘርፉ ስር በሚገኙት ተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ከሌሎች የሥራ ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የዉል ስምምነት ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ ማግኘት ባይቻልም በዘርፉ ስር የስራ ክፍሎቹ አንድ ላይ አቅደዉና ፕሮፓዛል አዘጋጅተዉ ስልጠና እንደሚሰጡ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ውስጥ ኦዲት ስራ ክፍል ለሥነምግባር መከታተያ እና ለህግ ክፍል የኦዲት ሪፖርት ተደራሽ ማድረጋቸዉን በተመለከተ አንዱ ተቋም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የኦዲት ሪፖርት የተላከ መሆኑን ከሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሌሎች ተቋማት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የኦዲት ሪፖርት እንደማይልኩና ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ብቻ እንደሚልኩ የተገኘዉ መረጃ ያሳያል፡፡

የሰዉ ሃይል በተሟላባቸውም የተቋማት የሕግ ክፍሎች ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ሥርዓት ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ ወይም አስተያየት የተሰጠባቸው ሰነዶች ማግኘት አልተቻለም፡፡ አሳታፊ ያለሆነ አሰረር በቅንጅት የሚሰሩ

ስራዎችን ጥራት የሚቀንስ ከመሆኑም ባሻገር ከሚመለከታቸው አካላት የሚሰበሰበውን ሙያዊ አስተያት እንዲሁም የእርስ በዕርስ የቁጥጥር ስርዓትንም የሚያዳክም ነው፡፡

ተቋማዊ አደረጃጀትን በተመለከተ በዘርፉ ስር በሚገኙ ተቋማት የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተሰጣቸውን ተልዕኮና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት እንዳለ ያሳያል፡፡ ሙስና ብልሹ አሰራር ለመከላከል አጋዥ ከሆኑት የስራ ዘርፎች መካከል የህግ አገልገሎት ክፍል አስተዋፅኦና ሚና ከፍተኛ ቢሆንም በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የህግ ክፍሉን በሚፈለገው ደረጃ አሳታፊ አለማድረጋቸው ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ስራን ዉጤታማ እንደማያደርግ ማየት ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- በአደረጃጃት በኩል የሚታየው መልካም ስራ መካካል የስነምግባር ክፍሉ በሰው ሃይል ለማሟላት የተደረገው ጥረት ነው፡፡ በአዋጁ መሰረት አሰፈላጊ የሰው ሃይል የመመደብ ተግባር በጥሩ ደረጃ ላይ መሆኑን መገነዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ክፍሉ በአዋጅ የተሰጡትን ሃለፊነቶችና ተግባራት ለመፈፀም የሚያስችል ሁኔታ ሊፈጥርለት እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ ይሁንጂ ክፍሉ የበጀት ነፃነት ያለው አይመስልም፡፡ ለክፊሉ ተብሎ የተመደበ በጀት አለመኖሩ ስራዎች በተቋም አመራር ውሳኔ ላይ የተመሰረቱ ያደርጋቸዋል፡፡ አመራሩ ስራው ስያምንበት በጀት የመፍቀድ ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ክፊሉ ስራው ያለጣልቃ ገብነት ሊሰራ መቻሉ አጠራጣሪ ነው፡፡ የስነምግባር ክፍሉ ከሌሎች የተቋም አደረጃጀቶች ጋር በቅንጅት የሚሰራበት መደበኛ አሰራር አለመኖሩም እንደ የአደረጃጀት ውስንነት ሊወሰድ ይችላል፡፡
- ሌላው ከአደረጃጃት ጋር ተያይዞ ሚታየው ውስነንነት የህግ ክፈሎች በሚፈለገው አቅም ደረጃ አመሆናቸው ነው፡፡ የሰው ሃይል ያልተሟላበት ሁኔታም ታይቷል፡፡ የህግ ክፍሉ ዋናው የሚጠበቅበት ሃላፊነት የምክር አገልግሎት መስጠት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም መረጃው በመሰብሰብ ሂደት የታየው ህግ ክፍሉ ውሎችም በመገምገም በኩል ያለው ተሳትፎ አለ ሊባል በሚችል ደረጃ አመሆኑ ነው፡፡ አንዱ ማሳያ የሕግ ክፍሎች ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ሥርዓት ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ ወይም አስተያየት የተሰጠባቸው ሰነዶች

ማግኘት አለመቻሉ ነው፡፡ ይህም የህግ በተቋማት ለመፈጠሩ የህግ ጥሰቶች የራሱ አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችለውን እድል አነስተኛ እንዲሆን ሊደርገው ይችላል፡፡

- የጥቆማ መቀበያ ስርአት መዘርጋቱ የሚያሳዩ መረጃዎች ቢኖሩም በጥቆማዎች ላይ ተመስርቶ የተወሰድ እርምጃ ስለመኖሩ የሚየያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ጥቆማዎችን መሰረት አድርጎ የእርምት እርምጃ መውሰድ ካልተቻል ተጠያቂነት ለማስፈን የሚደረገው ጥረት ደካማነት ሊያሳይ ይችላል፡፡ የተግልጋዮችም ሆነ የሰራተኞችን ሃሳብ ተቀብሎ መፈትሄ የመውሰድ ተነሳሽነትም የጎለ ክፍተት እንዳለው አመላካች ተደርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡

4.2. ተጠያቂነት

የሙስና ስጋት ጥናት በሚመለከት በዘርፉ ከሚገኙ ሶስት ተቋማት በአንድ ተቋም በንብረት አስተዳደር ዙሪያ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተካሄደ የአሰራር ሥርዓት ጥናት መካሄዱን በዚህ ጥናት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የሰነድ ፍተሻ ውጤት እንደሚያሳየው በንብረት አስተዳደር ዙርያ ጥናት በማካሄድ ብክነትን ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮች ለመዘርጋት ጥረት መደረጉን ለማየት ተችሏል፡፡ የጥናቱን ግኝቶቹን መሰረት በማድረግ በንብረት አስተዳደር ክፍል ካይዘን ተግባራዊ እንደተደረገ፣ ንብረት አያያዝና አስተዳደር ላይ ጥሩ ማሻሻያዎች እንደተደረጉ በዚህ ጥናት በተደረገ ምልከታና ሰነድ ፍተሻ ተረጋግጧል፡፡ ሌሎቹ ሁለት የዘርፉ ተቋማት የሙስና ስጋት ስርዓት ጥናት ስለማድረጋቸዉ ምንም ዓይነት መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በዚህ ረገድ የዘርፉ ተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ከሚጠበቅባቸው ተግባራት መካከል አንዱ የአሰራር ሥርዓት ጥናትን ማከናወን ሲሆን ጥናቱን ላለመሰረቱ ዋነኛው ምክንያት ሆኖ የቀረበው ተቋማቱ እንደ አዲስ የተደራጁ ስለሆኑ በቂ የሰው ሃይልና ጊዜ አልነበረም የሚል ነዉ፡፡

አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻልና ከደንበኞች ለሚነሱ ችግሮች መፈትሄ ለመስጠት በሁሉም የዘርፉ ተቋማት የደንበኞች እርካታ በገለልተኛ አካል ስለመጠናቱ አመላካች መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በሌላ መልኩ በዘርፉ ስር በሚገኙ በሶስቱም ተቋማት የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ያዘጋጁ መሆናቸውን በቀረቡ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ቢቻልም ደንቡ ከሶፍት ኮፒ ባሻገር በህትመት መልክ የተዘጋጀ ስለመሆኑና ለሚከለከታቸዉ አካላት ተደራሽ እንዲሆን የተደረገበት እንዲሁም በደንቡ ላይ ለሰራተኞች ስልጠናና ግንዛቤ ስራዎች የተሰሩበት አጥጋቢ ማስረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም፡፡ በዚህ ረገድ በዘርፉ በሚገኙ

ተቋማት ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ በበቂ ዝግጅትና በዕቅድ የተለዩ የግንዛቤ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

በኢንዱስትሪ ዘርፍ ስር የሚገኙ ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ቀርቦ የተደረጉ የቅድመ መከላከል ስራዎች እንደሌሉ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዘርፉ ተቋማት አንዱ በስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት በፈጻሚ አካላት ላይ የቀረቡ ክሶች መኖራቸውን ከሰነድ ማስረጃ ለማወቅ ቢቻልም በሌሎቹ ተቋማት በአመራሩም ሆነ በፈጻሚ አካላት ላይ የቀረቡ ክሶች ስለመኖሩ ሰነድ ማስረጃ አልተገኘም፡፡ በዘርፉ በሁሉም ተቋማት የህግ ክፍሉ ባለፉት ሁለት ዓመታት የመሰረታቸው ክሶች ስለመኖራቸው የሚያሳዩ የሰነድ መረጃ አልተገኘም፡፡

የቅሬታ አቀራርብ ስርዓትን በተመለከተ ዘርፉ ተቋማት ባለፉት ሁለት ዓመታት ከጂኤጂ ምደባ ጋር በተገናኘ ቅሬታዎች እንደቀረቡ የተገለጸ ሲሆን በሁሉም ቅሬታዎች ላይ ውሳኔ በማስተላለፍ ቅሬታዎችን መፍታት እንደተቻለ ከሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ ክፍሎች በተገኘው መረጃ መረዳት እንደተቻለው ከጂኤጂ ምደባ ባሻገር በአገለግሎት አሰጣጥና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ቅሬታዎች ቀርበው የተስተናገዱበት አሰራር እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለፀረ-ሙስና ትግል የአመራር ሚና ወሳኝ መሆኑን የተለያዩ የጥናት ውጤቶች ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የሰነድ ሪፖርቶች ማየት እንደተቻለው የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ አፈጻጸም ግምገማ እንደማንኛውም የስራ ክፍል ግምገማ ሲካሄድ አብሮ የሚገመገም ከመሆኑ ባሻገር ሙስና አሁን ካለበት አስጊ ገጽታ አንጻር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ክፍሉ ለብቻው በበላይ ሃላፊዎች የሚገመገምበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩን በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ በተተንተኑ ሀሳቦች በመነሳት

- የሙስና ስጋት ጥናት የመካሄድ ውስን ጥረት በዚህ ዘርፍ በአንድ ተቋም ታይቷል፡፡ሆኖም በሚፈለገው ደረጃ ጥልቀት ኖሮት የተካሄደ መሆኑን መረጃዎች አያሳዩም፡፡ ይሁን እንጂ የተገልጋዮች እርካታ ጥናት በማካሄድ ከአገልግሎት አኳያ የሚታዩ ሙሰና ስጋቶች የመለየት ስራ አለመሰራቱን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ጥናት

አለመደረጉ የሚያሳየው በመረጃና ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሙስናን የመዋጋት ስራ በተፈለገው ደረጃ እየተካሄደ አለመሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ታትሞ ለሚከለከታቸዉ አካላት በሚፈለገዉ ተደራሽ አለመደረጉና ተጠያቂነት ከማስፈን አንፃር ክፍተት እንዳለ ያሳያል፡፡ ደንቡ ተግባራዊች ተድረጎ ተጠያቂነት ማስፈን ካለተቻል መዘጋጀቱ ብቻ ስኬት አድረጎ መውሰድ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ሊያደርስ ስለሚችል፡፡ ስለሆኑም ከተደራሽነ ባሸገር ለተግባረዊነቱ ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው፡፡

4.3. የተቋማት ግልጽነት

ተቋማት ተግባሮቻቸውንና እንቅስቃሴያቸውን ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ አላማቸውን ለማሳካትና አፈፃፀማቸውን ለማሳደግ ሚናው የጎላ ነው፡፡ ግልፅነት ሙስናን ለማስወገድ ከሚያስችል መሰረታዊ ተግባራት አንዱ ነው፡፡ ይህን ለማሳካትም ተቋማት አሰራራቸውን ግልፅና አሳታፊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ዛሬ ተቋማዊ ግልፅነት ማስፈን ጠቃሚ የሙስና መከላከል መርህ ተደርጎ መውሰድ ተገቢ ያደርገዋል፡፡ ተቋማዊ ግልፅነት ማለት የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና አፈፃፀሞች መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚያቃልል ነው፡፡ ግልፅነትን የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳ መልካም ውጤት ቢመዘገብም ሂደቱ የተአማኒነት እና ቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ግልፅነት ለማስፈን እንዲያግዝ ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከማኔጅመንት አባላትና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እንደሚደረግባቸው ከሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከሁሉም ሠራተኞች ጋር ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ዙሪያ ውይይት የተደረገበት መሆኑን በቃል ቢገለፅም የቀረበ ማስረጃ ማቅረብ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ተቋማት የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ የ9 ወር ወይም ዓመታዊ ሪፖርቶች እንዳሏቸው እና የእቅድ አፈጻጻም ግምገማዎቹ የመልካም አስተዳር ችግሮችን ለመለየት ማስቻሉን በሪፖርቶች መመልከት ተችሏል፡፡

በዘርፉ ስር ያሉት ተቋማት ሁሉም ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ በማድረግ በኩል እየሰሩ መሆናቸውን ከቀረበው የሪፖርት አጻጸም ላይ ማየት ተችሏል፡፡ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚካሄድ ተሳትፎ እና ውጤትን ተደራሽ ማድረግን በሚመለከት የሚመለከታቸውን አካላት ከማሳተፍ አኳያ አሳታፊ የሚባል ቢሆን የውሳኔ ቃለ ጉባዔዎችን በተገቢው መንገድ ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ግን በደብዳቤ ብቻ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ተደራሽ መደረጉ ውስንነት ያለበት መሆኑን ያመላክታል፡፡ በዘርፉ ያሉ ሁለት ተቋማት የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በይፋ የሚያሰራጩ ሲሆኑ አንዱ በዘርፉ ያለ ተቋም ግን አዲስ የተደራጀና ህዳር 2015ዓም ስራ የጀመረ መሆኑን በመግለፅ የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በይፋ ስለማሰራጨታቸው የሚያሳዩ ሰነዶችን ማግኘት አልተቻለም፡፡

በዘርፉ ውስጥ ያሉ ተቋማት የማህበራዊ ሚዲያ የመጠቀም ልምድ እያዳበሩ መምጣታቸው መታዘብ ተችሏል፡፡ ተቋማት ዌብሳይት ያላቸው መሆኑን መመልከት ቢቻልም አጥጋቢ መረጃ የሚሰጡና በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎት እየሰጡ ናቸው ማለት አይቻልም (አሉ ከማለት በስተቀር) ፡፡ በሌላ መልኩ መረጃዎችን በሶሻል ሚዲያ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር በፌስቡክ ገፅ እና በቴሌግራም ቻናል መረጃዎች የማድረስ ስራም እየተሰራ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተለይ ለጨረታ ማስታወቂያ አዲስ ዘመን ጋዜጣን የሚጠቀሙ ሲሆን መረጃ ለማሰራጨት ግን የራሳቸውን ማህበራዊ ሚዲያ በብዛት ይጠቀማሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- አንዱ ከግልፅነት አኳያ እንደመልካም ልምድ ሊወሰድ የሚችለው ጉዳይ ቢኖር በእቅድና በጀት ዝግጅት ዙርያ አሳታፊ ለማድረግ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የተቋም ስራ አፈፃፀምም በየሩብ አመቱ የመገምገም ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ሆኖም ግምገማው ክፍተቶች በመለየት በኩል አስተዋፅኦ እንዳለው ቢመላከትም የተወሰዱ እርምጃዎች ስለመኖራቸው የሚሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ የሚያሳየው አመራሩ የሚስደው እርምጃ የማሳቅ ስራ አየሰራ አለመሆኑን ወይም ምንም የማስተካካያ እርምጃ አለመውሰዱን ነው፡፡ መረጃን ተደራሽ ከማደረግ አንፃር የተቋማት ዌብሳይቶች የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸው ስንታዘብ ለጉዳዩ ግልፅነት የማስፈን ሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡ አይደሉም፡፡

- በውሳኔዎች ላይ የማሳተፍ ሂደት በተቋመቱ ቢመላከትም የየውሳኔዎች ቃለ-ጉባኤዎች በልዩ ልዩ አማራጮች ተደራሽ የማድረግ ስራ ግን ደካማ መሆኑን ለመታዘብ ተችሏል፡፡ ውሳኔዎች አላግባብ ሲወሰኑ ቃለ ጉባኤዎች ተደራሽ አለመሆናቸው ቅሬታ ለማቅረብ አዳጋች ያደርገዋል፡፡ ይህም ውሳኔ ሰጪው አካል ስልጣኑን ተጠቅሞ ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ ሲያሳልፍ አሳታፊና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ስተቱን እንዳያርም ሊያደርገው ይችላል፡፡ ውጤቱም ስልጣንን አላግባብ ጥቅም ላይ ማዋል ሊያስከትል መቻሉ መገንዘብ ተገቢ ያደርገዋል፡፡
- ተቋማት የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም ስለሚሰሯው ስራዎች ተደራሽ የሚያደርጉ መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም ሙስና እና ብልሹ አሰራር በመከላከል ረገድ ባለድርሻ አካላትና ዜጎች ስላላቸው ሊያደርጉ ስለሚችሉ ተሳትፎ አለመታወቁ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል መረጃዎችን ለማግኘት አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡

4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመታገል ከሚያስችሉ መሳሪያዎች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ያላቸዉ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ የየተቋሙ አመራሮችና ባለሙያዎች ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታቸውን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በጥናቶች እና ዕለት-ከዕለት ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች በመነሳት አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት እየተሰራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ተቋማት የስነ-ምግባር ደንቦችና ሙስና መከላከል የሚያስችሉ መመሪያዎች በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አዋጅና መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር በማስመዝገብ ተመሳሳይ መመሪያዎች በተለያዩ ተቋማት በአንድ ጊዜ በተለያየ ትርጉም እንዳይሰጣቸው ለማድረግ የተሰራ ስራ መኖሩን ከተገኙት መረጃዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን በዘርፉ ስር ካሉት ተቋማት መካከል ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና እየተሰጡ መሆኑን የሚያመላክት መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ፀድቀው የሚወጡ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ በማህበራዊ ሚዲያዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን ከተቋማቱ በተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡

በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት አንዱ ብቻ አዲስ የተደራጀ በመሆኑ የዜጎች ቻርተርን በማዘጋጀት ለተገልጋዮች ተደራሽ ያላደረገ ሲሆን ሌሎች ተቋማት የዜጎች ቻርተርን በማዘጋጀት ለተገልጋዮች ተደራሽ ያደረጉ ቢሆንም በሚፈለገዉ ልክ ተ አለመሆኑን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- በዘርፉ ተቋማት አስፈላጊና ናቸወ የሚባሉ አዋጆች መመሪያዎችና ደንቦች በማዘጋጀትና ማሻሻል በኩል ያለው እንቅስቃሴ እንደጥሩ ልምድ መውሰዱ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ተቋማት በአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እየተሰራ ስለመሆኑ መረጃችዎች አልተገኙም፡፡ ግንዛቤ መፍጠር አለመቻሉ ውጤታማ የመከላክል ስራ ተግባራዊ ለማድረግ አዳጋች ሊያድገው መቻሉ ግምት ውስጥ በማሰገባት የግብዛቤ ማሰጨበጫ መድረኮች ወይም ስልጠናዎች ማካሄድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በተጨማሪም የወጡት አዋጆች መመሪያዎችና ደንቦች ተግባር ላይ ስለመዋላቸው ክትትል የመድረግ ስራ ከተቋም አመራሮች ይጠበቃል፡፡
- የዜጎች ቻርተር ተዘጋጅቶ በተገቢው መንገድ ለተገልጋዮች ተደራሽ አለመደረጉና ተገቢ የትግበራ ክትትል ስለመደረጉ የሚሳዩ መረጃዎች አልቀረቡም፡፡ ይህ ተጋባራዊ አለመደረጉ ግልፅነትና ተጠያቂነት ከማስፈን አንፃር ሲታይ የሚደረግረ እቅስቃሴ ደካማ መሆኑን ነው፡፡

4.5. የንብረት አስተዳደር

በመንግስት ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከሚስተዋልባቸው መንገዶች አንዱ የንብረት አያያዝ፣ አስተዳደር እና ማስወገድ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህን ለመከላከል

ከተቀየሱት መንገዶች መካከል የንብረት አስተዳደሩን በዘመናዊ አሰራር መቀየር መሆኑን በመንግስት የታመነበት ነው፡፡ በዘርፉ አዲስ ከተደራጀ አንድ ተቋም በስተቀር የንብረት አስተዳደር ስርዓትን በተመለከተ በቀረቡት ሰነዶች ማረጋገጥ እንደተቻለው ተቋማቱ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ስራ እየሰሩ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የካይዘን ስርዓት አተገባበር እና የተገዙ እቃዎች የግዥ መመሪያ ሥርዓት የተከተሉና በሠነድ እየተመዘገቡ መረጃዎች በአግባቡ እንዲደራጁ ከማድረግ አንፃር የተሰራው ስራ በጥሩ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት የተደረጉት የሰነድ ፍተሻዎች ያሳያሉ፡፡

በዘርፉ ስር ካሉት ተቋማት በአንዱ የሚወገዱ ንብረቶች በባሙያዎች የመለየት ስራ ስለመስራታቸዉ፣ ተገቢ ጥበቃ እና አያያዝ እንደሚደረግላቸዉ እና በደህንነት ካሜራ እንደሚጠበቁ፣ እንዲሁም በግልፅ ጨረታና በስጦታ(በድጋፍ) መልክ በሚመለከተው አካል ፀድቆ የማስወገድ ስራ እንደሚሰራና እየተሰራ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በቀሪ ሁለት ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶችን በባሙያዎች የመለየት ስራ ስለመስራታቸዉና ህጉን ጠብቀው ስለመወገዳቸው የሚያሳይ የሰነድ መረጃ አልተገኘም፡፡ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በነበረዉ ውይይት እንደተገለፀው በሁለቱ ተቋማት በስቶር እጥረት ምክንያት በማዕከል ያሉ የሚወገዱ ንብረቶች ተገቢ ጥበቃ እና አያያዝ እየተደረገ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና በመነሳት፤

- ዘርፉ በቅረብ የተደራጀ እንደመሆኑ ብዙ አስተያየት መስጠት ቢከብደም የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓት በተሟላና በተደራጀ ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑ ለመመልከት ተችሏል፡፡ በአውቶሜሽን የታገዘ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርኣት አለመዘርጋቱ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር በር ከመክፈት ባሻገር የሀብት ብክትን ሊያባብሰው ይችላል፡፡ በስቶር እጥረት ምክንያት በማዕከል ያሉ የሚወገዱ ንብረቶች ተገቢ ጥበቃ እና አያያዝ እየተደረገ አለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆን የመንግስትና ህዝብ ሃበት ለብክነት እንዳይጋለጥ በካይዘንና ንብረት ጥበቃ ዙርያ ተቋማት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ ይገባቸዋል፡፡ ይህ ማድረግ ከተቻለ ግን ሃለፊነታቸው በመወጣት በኩል ክፍተኛ ጉድለት መኖሩ ለመስና ስጋት አመላካች ተድረጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.6. የግዥ አስተዳደር

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ሟሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የዕቃና የአገልግሎት ግብአቶችና መሳሪያዎች ለሟሟላት የግዥ ስርአትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል፡፡ የግዥ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናቱ እንደሚከተለው ተንትኖታል፡፡

በዘርፉ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት የግዥ እቅድና አፈፃፀም ግምገማ እንደሚካሄድ መረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን ግምገማ የሚካሄድዉ የስራ ክፍሉን ለብቻዉ ሳይሆን የሌሎች ስራ ክፍሎች እቅድና አፈፃፀም ሲገመገም አንድ ላይ መሆኑን በሰነድ ፍተሻ ተረጋግጧል፡፡ በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት ግዥ የሚከናወነው በእቅድ፣ ከየክፍሉ ያለን ፍላጎት መሰረት በማድረግ እንዲሁም ስቶክ ላይ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ስለመሆኑ በተደረገ ውይይት እና በቀረቡ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ተቋማቱ ከየክፍሉ የሰበሰቡትን ፍላጎትና በተቋም ደረጃ የሰሩትን ማጠቃለያ የሚያሳይ መረጃ ቢያደራጁ ለመረጃ ፈላጊ አካልና ለሚመለከታቸው አካላት ግልፅነትን ከማስፈኑ በተጨማሪ የግዥ ስርዓቱ ህግና ስረዓት በማስያዝ በዘፈቀደ የሚገዙ ግዥዎች ሊያመጡ የሚችሉትን የሙስና ስጋት ይቀንሳል፡፡

በዘርፉ ከግዥ በፊት የገበያ ጥናት እንደሚያደርጉ ቢመላከትም የገበያ ጥናት አድራጊ ኮሚቴም ማደራጀታቸውን የሚያሳይ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ EGP በተመረጡ ድርጅቶች እንዲተገበሩ በያዘው አቅጣጫ መሰረት በዘርፉ ስር ባሉ መስሪያ ቤቶች የአተገባበር ስራዉ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ግዥ በማኑዋል የሚፈጽም ተቋም መኖሩንም ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ የግዥ ስርዓት ሀብትን በቁጠባ ለመጠቀምና የግዥ ሥርዓቱን በእቅድ ከመምራት አንፃር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ሲሆን ያላጠናቀቁ ተቋማት የማዘመኑን ስራ በማጠናቀቅ ቀድሞ ከነበሩበት የማንዋል ሥራ ወደ ዲጂታል ሲስተም በፍጥነት እንዲዛወሩ ግፊት ያስፈልጋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና በመነሳት፤

- የግዥ ስራ ክፍል ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ከሆኑ የስራ ሂደቶች ቀዳሚ እንደመሆኑ መጠን የግዥ እቅድና አፈፃፀም ግምገማ ለብቻዉ ትኩረት ተሰጥቶት

እየተደረገ አለመሆኑ ነው፡፡ ግምገማ አለመደረጉ የሚገዙ እቃዎች ግልፅነት ባለው መንገድ መገዛታቸው ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በተጨማሪም የዲጂታል ሲስተም የግዥ ስርዓት አለመጠናከሩ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ የሚችል እድል መኖሩን አመላካች ነው፡፡

- የገበያ ጥናት መካሄዱ ቢመላከትም ይህን ጥናት የሚያካሂድ አካል አለመደራጀቱ ለመመልከት አልተቻልም፡፡ ይህ የሚያመላክተው ጥናት አለመካሄዱ ወይም አጥኚው ቡድን የሚፈለገው እውቀትና ክህሎት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም የገበያ ጥናት ስራው መደበኛና ተከታታይነት ባለው መልኩ እየተካሄደ አለመሆኑም ያሳያል፡፡

4.7. የሰው ሀብት አስተዳደር

የአንድን ተቋም ስኬትና ውጤታማነት ከሚወስኑ መስረታዊ ግብኣቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያላቸው የሰው ኃብት ልማት አስተዳደር ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር የሙስና ስጋት ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ የቅጥር ማስታወቂያዎች በጋዜጣ እንዲሁም የውስጥ ሰሌዳ ላይ እንዲለጠፍ በማድረግ ተደራሽ መደረጉን በተደረገው ምልከታ/የሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ተቋማት የዲሲፒሊን፣ የቅሬታ ሰሚ ፣ የቅጥር/ምደባ ኮሚቴ በማቋቋም ስራ እየሰሩ መሆኑን ከተቋማት የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ስር ባሉት ተቋማት የቀረቡ ቅሬታዎች በሙሉ ዉሳኔ እንዳገኙ የሰነድ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ በዘርፉ ቅሬታዎችን በማስተናገድ እና መፍትሔ በመስጠት በኩል አመርቂ ሊባል የሚችል ስራ መሰራቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሰራተኛ እና አመራር የሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ማጣራትን በተመለከተ ተግባራዊ መደረጉን ሊያሳይ የሚችል ማስረጃ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም ከስራ ክፍል ኃላፊዎች ጋር በነበረዉ ውይይት የማጣራት ስራ እንዳልተሰራ እና ስራውን ለመጀመር በሂደት ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የሰራተኛ እና አመራር ምደባም በህጉ መሰረት እየተፈፀመ መሆኑን የሚያሳዩ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ ተግኝተዋል፡፡ የመካከለኛ አመራር ምደባ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና

ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የሰራተኞች ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆንም ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት የተዘረጋ መሆኑና ሕጉን በተከተለ መልኩ እየተሰራ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተቋማቱ ውስጥ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት መረጃ ስርዓት የማደራጀት ጅምር ስራዎች እንዳሉ እና ከተተገበሩ ሲስተሞች ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከተገኙ ሰነዶች መረጃ ማረጋገጥ እንደተቻለዉ ተቋማት ትኩረታቸው የአቅም ግንባታ ላይ ሲሆን ለሥነ-ምግባር ስልጠና የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎችም ቢሆኑ በስልጠና ፍላጎት ጥናት ላይ ተመስርተው ስለመሆኑ የሚያመላክቱ መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- የሰራተኛው ማህደር የማጥራት ስራ ሙስናን ለመከላከል አንዱ መሳሪያ ሆነ ሊያገለገል ይችላል፡፡ የማጥራት ስራው በዋናነት የሚካሄደው ድግሞ የትምህርት ማስረጃ እና ስራ ልምድ የማረጋገጥ ስራ ሲሰራ ነው፡፡ ሆኖም በጥናቱ የተካተቱት የዘርፉ ተቋማት ማስረጃወችን የማረጋገጥ ስራ አለመስራታቸው ነው፡፡ ይህ አላግባብ የውሸት ሰነዶች ላይ ተመስርቶ ለሚፈፀም ሙሰና ስጋት ተቋማቱን ተጋላጭ ያደርጋቸዋል፡፡
- ስልጠና ሙሰናን ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ተጋባራዊ ማደረግ ላይ ወስንነት እንዳለ ከምልከታው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ተቋማቱ የሰራተኛውን ስነምግባር በማሻሻል በኩል አስተወፅኦ ሊኖራቸው የሚችሉ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት የአመለካካት ለውጥ ለማምጣት የሚያደርጉት ጥረት ደካማ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ የአመለካካት ለውጥ ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ለቅደመ መከላከል ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥርዓት ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ዓይነተኛ መሳሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ለዚህም በሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ አዋጅ ቁጥር 668/2002 መሰረት በሃገራችን ላለፉት ዓመታት የመንግስት ሰራተኞች፣ ባለስልጣንና ተመራጮች ሃብታቸውና ንብረታቸውን ማሳወቅና ማስመዝገብ እንዳለባቸው የህግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

በመሆኑም በዘርፉ በተካተቱ ተቋማት መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የሰራተኞችና ባለስልጣናት ሃብታቸውን ማሳወቅና የማስመዝገብ ስራ በተሻለ ማከናወን መቻሉ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም 98% አፈጻጸም ማስመዝገብ ችሏል፡፡ በዘርፍ ውስጥ ካሉ ተቋማት መካከል ሁለቱ እንደ አዲስ የተደራራጁ በመሆናቸው የተደራጀ የሀብት ምዝገባ ሰነድ መኖሩን የሚያሳይ ሰነድ ባይኖርም ሰራተኞቹ አዲስ ወደተቋቋሙ ተቋማት ከመምጣታቸው በፊት ሃብታቸውን ማስመዝገባቸውን ግን በቃል ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም አዳዲሶቹ ተቋማት ከሽግግር በኋላ የሃብት ምዝገባ ስራ ቢጀምሩም በስሲተም በመሆኑና ሲስተሙ ተደራሽ ባለሆኑ ችግር እንዳጋጠማቸው ገልፀዋል፡፡

ከትንተናው መግንዘብ የሚቻለው ነገር ቢኖር፤

- የሃብት ማሳወቅ እና ምስገባ ስራ ላይ በዘርፉ ያሉት ተቋመት ያሳዩት አፈፃፀም ለጉዳዩ ምንያክል ትኩረት እንደተሰጠው ያሳያል፡፡ ሁሉም ሰራተኛ በሚባል ደረጃ ሃብቱን የማሰመዝግብ ሰራ ተሰርቷል፡፡ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓት የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና ምንጫቸው ያልታወቀ (ተገቢ ያልሆኑ) ንብረቶችን ለመለየት ካለው ፋይዳ አንፃር በዘርፉ ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በምዝገባው ላይ ተመስርቶ ተጠያቂነት የማስፈን ስራ ቢሰራ አፈፃፀሙን አሰተማሪ በሆነ መንገድ ሙስናን የመከላክል ስራው አንድ እርምጃ ወደፊት ሊያራምደው ይችላል፡፡

4.9. ኦዲትና ቁጥጥር

በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት በየአመቱ የውስጥ ኦዲትና ቁጥጥር ስራ እየሰሩ መሆናቸዉን በተደረገው ምልከታና የሰነድ ማረጃ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የውጪ ኦዲት ሪፖርት በሂደት ላይ በመሆኑ መረጃዎች ማግኘት ባይቻልም በተቋማቱ የውስጥ ኦዲት ግን በየጊዜው ኦዲት እንደሚደረግ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም የተቋማቱ አመራር የውስጥ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ እንደሚያካሂድና የተገኙ ግኝቶች ላይ ተመስርተው ማሻሻያዎች ስለመደረጋቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዘርፉ ያሉ ተቋማት በኦዲት ግኝቶች ላይ ማሻሻያዎች የሚያደርጉ ሲሆን ለማስረጃነት ከገንዘብ ሚኒስቴርና ዋና ኦዲተር መ/ቤት ጋር የተደረገው የመረጃ ልውውጥ ደብዳቤ እና በተቋሙ የውስጥ አዲተሮቾ በየሩብ አመቱ የሚደረጉ ውይይቶች ላይ የታዩ ማሻሻያዎች

በቃለ-ጉባኤ በአባሪነት ቀርቧል፡፡ ነገር ግን የኦዲት ሪፖርቶቹ ለሁሉም የስራ ክፍሎች ተደራሽ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ የኦዲት ሪፖርት ተደራሽነትን በተመለከተ በዘርፉ ካሉ ተቋማት አንዱ ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል፣ለፋይናንስና ግዥ እና ለንብረት አስተዳደር ተደራሽ የሚያደርግ ሲሆን ለሌሎች የስራ ክፍሎች ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር ልምድ አለመኖሩን ከቃለ ጉባኤዎችና ከተጻፉ የኦዲት ሪፖርት ደብዳቤዎች ለማየት ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ የሌሎች ተቋማት የኦዲት ባለሙያዎች የኦዲት ሪፖርቶችን ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍልና ለሌሎች የስራ ክፍሎች ተደራሽ እንደማያደርጉ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- በተቋማቱ የውስጥ ኦዲት በየጊዜው ኦዲት እንደሚደረግ መረጃዎች ያሳያሉ በተጨማሪም የተቋማቱ አመራር የውስጥ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ ያካሂዳሉ ሆኖም ግን በተሟላ መልኩ ለሥነምግባር መከታታያ ክፍሎችና ለሌሎች ተደራሽ አለመደረጉ ሙስናን በቅድሚያ ለመከላከል አለማስቻሉን ያሳያል፡፡ የኦዲት ግንኝት መረጃውች ባግባቡ ተደራጅተው አለመቅረባቸው የመረጃ አያያዝ እና ተደራሽነት ላይ ክፍተት ያለ መሆኑን ማሳያ ነው፡፡ በተጨማሪም የኦዲት ሪፖርቶች ላይ ተመስርተው የተወሰዱ የእርምት ስራዎች ተጠያቂነት በማስፈን በኩል ያበረከቱት አስተዋፅኦ በግልፅ የሚያሳዩ መረጃዎች አለመኖራቸው ሙስናን ለመዋጋት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስንነት እንዳለባቸው አመላካች ነው፡፡ ስለዚህ ሪፖረቶቹ ተደራሽ ከመደረጋቸው ባሻገር ተጠያቂነት በሚያረጋግጥ መልኩ ጥቅም ላይ ካልዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመዋጋት ያላቸው ፋይዳ ጎዶሎ ያደርገዋል፡፡

4.10. የዘርፉን የሙስና ሥጋት ማሳያዎች ልየታ

የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ማለት ታሳቢ ስጋት ሲሆን ቢከሰት የተቋሙን የአሰረር ስርዓት አደጋ ላይ የሚጥል እና ማህበረሰቡ በተቋሙ ላይ ያለውን አመኔታ የሚሣጣ ሲሆን በተደጋጋሚ በሚከሰት ብልሹ አሰራር ድግግሞሽና እና ብልሹ አሰራሩ ቢከሰት ሊፈጥር በሚችለው ተፅዕኖ ምክንያት የሚለካ ስጋት ነው፡፡ በመሆኑም ዘርፉ ባለው የስራ ባህሪ፣ ከሚያንቀሳቅሰው ሃብትና ከሚከተለው የአሰራር ስርዓት አንፃር በተቋሙ ውስጥ ስለተቋሙ በቂ መረጃና ልምድ ያላቸው የተጠመረጡ የዘርፍ መራሮችና ባለሙያዎች በሰጡት መረጃ መሰረት የዘርፉ የሙስና ስጋት ይሆናሉ ያሏቸውን አሰራሮች እንደሚከተው ሰጥተዋል፡፡

በዚህም መሰረት የግዥ አገልግሎት ከፍተኛ፣ የንብረት አስተዳደር መካከለኛ፣ ተሸከርከሪን በተመለከተ (ስምሪት፣ነዳጅ አጠቃቀምና ጥገና) መካከለኛ፣ የፋይናንስ አገልግሎት መካከለኛ፣ የሰዉ ሀብት ልማትና መካከለኛ፣ የገበያ ልማትና የኢንዱስትሪዎች ትስስር መካከለኛ ስጋቶች መሆናቸው ተመላክቷል፡፡

ምዕራፍ አምስት

መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳቦች

5.1. መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የነበረው፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመዳሰስ የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ በዚህ አቢይ ዓላማ ስር በጥናቱ መቋጫ ላይ ምላሽ ያገኛሉ ተብለው የታሰቡ አምስት የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህም፡- 1ኛ. የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣ 2ኛ. የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣ እና 3ኛ. ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በሪፖርቱ ላይ ከቀረቡትን አበይት የጥናቱ ውጤቶች መሰረት በማድረግየሚከተለው ድምዳሜ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

1. በዘርፉ ያሉት የስነምገባር ክፍሎች በሰው ሃይል እና በተለያዩ ግብአቶች የተሟሉ መሆናቸው ተቋማት በአዋጅ የተጣለባቸወን ሃላፊነት ለመወጣት ጥረት ማድረጋቻው ያሳያል፡፡ ሀኖም ስነምግባር ክፍሉ የበጀት ነፃነት ያለው አይመስልም፡፡ ይህ አቅዶ ስራው እንዳይሰራ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተደራጀ መልኩ ለመዋጋት የሚያስችል ቅንጅታዊ ስራ እየተሰራ አመሆኑን ታይቷል፡፡
2. በሙስና ስጋት ዙርያ እና በተገልጋዮች እርከታ ላይ ጥልቀት ያላቸው ጥናት የማካሄድ ልምድ አለመዳበሩ በጥናት ላይ የተመሰረተ ተቋማዊ ተጠያቂነት ስራ እየተሰራ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡
3. እስከ ታችኛው የተቋም ክፍሎች መረጃ ተደራሽነት ስራ አጠጥጋቢ በሚባል ደረጃ አለመሆኑን ለማስተዋል ተችሏል፡፡ የእቅድና አፈፃፀም መረጃዎችና ሪፖረቶች በከፍተኛና መካከለኛ አመራሩ አከባቢ ላይ ተንጠልጥሎ የመቅረት አዝማሚ መኖሩን ይታያል፡፡ ፡
4. በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ዙርያ ለአስፈፃሚው አካል ስለጠና የመስጠት ልምዱ የለም በሚባል ደረጃ ላይ መሆኑን ነው፡፡
5. በተቋማቱ ያለው የንብረት አስተዳደር ለማዘመን የሚያስችሉ የካይዘን ስርኣት እና የአውተሜሽን ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተስተውሏል፡፡
6. በዘርፉ ተቋማት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ተስተውሏል፡፡

7. በዘርፉ ባሉ ተቋማት የአስፈፃሚው ስነምግባር ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ ስለጠናዎች አየተሰጠ አመሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡
8. ሃብት በማሳወቅና ማስመዝገብ ስራ ዙሪያ የተሰራው ስራ ትልቅ ስኬት ማሳያነው፡፡ ይህም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት መረዳት ተገቢ ነው፡፡
9. የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች በቀላሉ ተደራሽ አለመሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮች እና ሙሰናን ለመዋጋት የሚስችል ሁኔታ አለመፈጠሩ ነው፡፡

5.2. የመፍትሄ ምክረሃሳቦች

ከላይ ከቀረበው ትንታኔ እና ድምዳሜ አኳያ የሚከተሉት ምክረሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

- የስነምግባር ክፈሎች ስራቸውን በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርጉ የበጀት ነፃነት እንዲኖራቸው ቢደረግ የተሻለ ስራ እንዲሰሩ ሊያግዛቸው ይችላል፡፡
- መስናን የመዋጋት ስራ የተቋም አመራር ሃፊነት መሆኑን በመገንዘብ አመራሩ የስነምግባር ግንባታው እና የመከላከል ተግባር በተደረጃ እና በተጠናከረ መልኩ ሊመራው ይገባል፡፡
- ሙስናንና ብልሹ አሰራር ለመዋጋት ፋይዳ ያላቸው የስራ ክፍሎችን በቅንጅት የሚሰሩበት ስራ የማመቻቸት ስራ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ስለሆነም የተቋማት ኃላፊዎች፣ የህግ፣ የለውጥ፣ የውስጥ ኦዲትና የስነመግባር መከታያ ክፍሎችን አቀናጅቶ መጠቀም የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጉና አፈጻጸማቸውንም ሊገመግሙ ይገባል፡፡
- የሙስና ስጋት እና የተገልጋዮች ጥናት በማካሄድ ችግሮችን ለይቶ ተጠያቂነት የማስፈን ስራም ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡
- የንብረት አስተዳደሩ እና የግዥ ስራአቱ በአውቶሜሽን የማዘመን ስራ ተግባራዊ ማድረግ ከተቋማት ይጠበቃል፡፡
- የመረጃ አያያዝ እና ስርጭት ላይ ግልፅነት በሚያሰፍን መልኩ የማዘመን ስራ መስራት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- ሃብት የማሳወቅ እና ምዝገባ ስራውም በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ማደረግ ያለው አፈፃፀም ቀጣይነት እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡

- የሰው ሃብት አቅም ግንባታ ስራ በተጨማሪም የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስጃዎች ማጥራት በትኩረት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡
- የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የማድረግ ስራ መስራት አለበት፡፡

Reference

2. Chakravorty, N N Tarun, Vladislav Rutskiy and Elena Sevastyanova (2022) Does corruption have an impact on industrial growth? Evidence from Russia, South Florida Journal of Development, v.3, no.4. pp. 5132-5150, jul./aug. Miami USA. (file:///C:/Users/Mohamed/Downloads/082+SFJD.pdf)
3. Williams, C.C. and Martinez-Perez, A. (2016) Evaluating the impacts of corruption on firm performance in developing economies: an institutional perspective. International Journal of Business and Globalisation, 16 (4). ISSN 1753-3627
4. Deloitte LLP (2020) Economic crime in the manufacturing sector New Street Square, London United Kingdom.
5. Tingvall , Patrik Gustavsson (2010, December) Offshoring and Corruption: Does Corruption Matter, The Royal Institute of technology Centre of Excellence for Science and Innovation Studies (CESIS)